# የኢሚሬት ባህል



P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E
www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

# የኢሚሬት ባህል

ባሕል አንድ ህብረተሰብ ከሚገለጽበት ባህርይ አንዱና ዋነኛዉ ነው። የማህበረሰቦች ማንነት የሚገለጽበት ምንጭ ሲሆን ተስፋቸውን በመገንባት ለወደፊት በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ያስችላል።
የተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ ባህል ለየት የሚያደርገዉ ከማህበረሰቡ መሰረታዊ ልምዶችና መርሆዎች የተዉጣጣ መሆኑ ነው።

ባህሉ በአሥር ወይም ሃያ ዓመታት ውስጥ የተመሰረተ ሳይሆን የሃገሪቱ ዜጎች ግባቸውን እና ምኞታቸውን ለማሳካት በሰብአዊ ችሎታቸው ውስጥ ባደረጉት ቅርሳዊ ተሳትፎ ነዉ ።
የኢሚሬት ባህል ከእስልምና ትምህርት እና መርሆዎች የተወሰደ እንደመሆኑ መጠን የህዝቦቿ ባህርይ በእስላማዊው አስተምህሮቶች የታነጸ ነዉ ።ይህም በሁሉም የህይወት ገጽታዎቻቸዉ ይታያል በተለይ ደግሞ የኢሚሬት ህዝቦች ከሌሎች ህዝቦች ጋር አብሮ በሰላምና በመቻቻል መኖር እና በዉስጧ የተለያየዩ ዜጎች በፍትህ እና በእኩልነት የሃይማኖታዊ ሥርዓቶቻቸውን እንደልብ የማከናወን ፍጹም ነፃነት አላቸዉ ።

በሌላ በኩል የኢሚሬት ባህል ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከኢሚሬት ሕዝቦች ባህልና ልማድ ጋር የተሳሰረ ስለሆነ ቤተሰብ በኢሚሬት የመጀመሪያው የህብረተሰብ ክፍል ነዉ።ቤተሰባዊ ስብዕናና ማኅበራዊ ትስስር ከአያቶች የተወረሰ ቅርስ ሲሆን እውነተኛ ማህበረሰባዊ አንድነትን ያንጸባርቃል።ስለሆነም የአንድ ግለሰብ ኃላፊነት ከቤተሰቦቹ አልፎ መላውን ሰፈር ያካትታል።ይህ ሥርዓት በዘር እና በጎሳ መካከል ምንም አይነት ልዩነት ሳይፈጥር በማህበራዊ አንድነት ሃሳብ ላይ ብቻ በማተኮር እንደ ጋብቻና ክብረ በዓላት በሚሮር ገዜ የገንዘብና የማህበራዊ ድጋፍ በማድረግ በቅን ልቦና መሳተፍን ያበረታታል።

ይህ ማህበረሰባዊ ጥምረት እና መተባበር በ 1971ዓ.ም የተባበሩት የዓረብ ኢሚሬትስን ፈጥሯል።
ይህ የአንደነት መንፈስ የፈለቀዉ ከሃገሪቱ ህዝቦች ጥምረትና ትስስር ሲሆን የመሥዋትነትና የሃገር መከላከልን ስሜት የተላበሰ ነዉ። የኢሚሬት ሕዝቦች የዚህ ሃገር አካል በመሆናቸዉ ከፍተኛ ኩራት ይሰማቸዋል ለመሪዎቻቸዉም ታላቅ እምነት አላቸዉ። ይህ የአገር ፍቅር ስሜት ኢሜሬትን ከሌላ አገር ለየት ያደርጋታል።

ዛሬ ኢሚሬቲስ ከዓለም አቀፋዊነት ጋር በመጣጣም ዘመናዊ ህይወትን የምትመራ ሲሆን በዘመናዊው የኑሮ ደረጃ ላይ በመታገዝ  የብሄራዊ ማንነቷን በመጠበቅ እድገትን ተጎናጽፋለች ።
የኤሚሬትስ ፕሬዚዳንት አባታችን ሼክ ኸሊፋ ቢን ዛይድ አል ነህያን "ማንነቱን ያላወቀ ሰው አሁኑም ሆነ ወደፊትም ቦታ የለውም" ብለዋል።

በቅርብ ዓመታት በኢሚሬትስ ከፍተኛ የባህል እንቅስቃሴን ተመልክተናል ።መንግስት በሀገሪቱ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የተንሰራፋውን የሳይንስ ግስጋሴ  ለመከታተል ድርጅቶችንና ተቋማትን መስርቷል። እነዚህ ተቋማት የአገሪቱን የወደፊት  ዕድገትን፤ ፈጠራን እና ክህሎትን ለማጎልበት በሚደረጉ ጥረቶች እና አስተዋፅኦዎች ያበረታታል።